የወ/መ/ቁጥር 123526

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረቡ

ተከሳሽ፡ አቶ ኦሪ ብዛ ዳርጌ - ከጠበቃ አቶ ተማም አባቡልጉ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

ፍርድ

ዐ/ሕግ ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 346 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ መጋቢት 05 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ክልል ልዩ ቦታው ጋንዲ ሆስፒታል ፊት ለፊት ከሚገኘው ቤት ቁጥር 375 ከሆነው ሱቅ ውስጥ የ21 የውጭ አገራት ገንዘቦችን እና የኢትዮጵያን ብር በሕገወጥ መንገድ በማከማቸቱ እና በመመንዘሩ በፈፀመው በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ መነገድ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ ሁለት ምስክሮችን እና የሰነድ ማስረጃ አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ምስክሮቹ በሰጡት ቃል በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ በወቅቱ በተከሳሽ ሱቅ ሕገወጥ የሆነ የገንዘብ ምንዛሬ ይሰራሉ ተብሎ ከፍ/ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ ወጪ በማድረግ ቤቱ ውስጥ በመግባት ፍተሻ ሲያደርጉ በክሱ ላይ በተገለፀው መልኩ የ21 የውጭ አገራት ገንዘብ በሱቁ በተለያዩ ቦታዎች ማለትም በመሳቢያዎች፤ በኮርኒስና በግድግዳዎች ተቀምጠው እንደተገኙና ይህን ገንዘብ ይዘው መሄዳቸውን ሲያስረዱ፤ ተከሳሽ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 27(2) መሰረት በፖሊስ ጣቢያ ቀርበው በሰጡት ቃልም በክሱ ላይ የተመለከተውን የውጭ አገራት ገንዘብ መመንዘር ስራውን ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ሲያከናውኑ እንደነበር አምነው ቃላቸውን ሰጥተዋል። ከዚህ ሌላ የውጭ አገራት ገንዘብን የመመንዘር ሥራ ለግለሰቦች ያልተፈቀደ መሆኑን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የፃፈውን ደብዳቤ አያይዞ አቅርቧል። ፍ/ቤቱም እነዚህን ማስረጃዎች መርምሮ የዐ/ሕግ የሰነድና የሰው ማስረጃዎች እንደ ዐ/ሕግ ክስ ያስረዱ ስለሆነ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 346 ስር እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዟል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብለው ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገፅ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም የዐ/ሕግ ምስክሮች የገለፁት እና በሕጉ ላይ የተገለፀው አንድ አይነት ባለመሆኑ በነፃ እንድሰናበት፤ በሕጉ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ ተከሳሽ አልጣሰም፤ በውጭ አገር ገንዘብ እየነገድኩ የነበረ ስለመሆኑ አንዳቸውም ማስረጃዎች አላረጋገጡም፤ የውጭ አገርን ገንዘብ ይዞ መገኘትም ወንጀል አይደለም፤ የኢትዮጵያ ብርንም ይዞ መገኘት ወንጀል ስለመሆኑ የተጠቀሰ ድንጋጌም የለም፤ በአጠቃላይ የዐ/ሕግ ማስረጃዎች ከጥርጣሬ በፀዳ መልኩ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸውን ያላስረዱ በመሆኑ በነፃ እንድንሰናበት በማለት ፅሑፍን አጠቃለዋል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ አስተባብሏል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 346 ርዕሱ በወርቅ፤ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ መነገድ የሚል ሲሆን በውስጡ ግን ዝርዝር ነገሮችን የያዘ ነው። ከእነዚህ ውስጥ ማናቸውንም የውጭ አገር ገንዘብ፤ ፈቃድ ሳኖረው ወይም ሕግን በመጣስ የገዛ፤ ከውጭ አገር ያስመጣ ወይም ወደ ውጭ አገር የላከ፤ በአደራ አስቀማጭነት የተቀበለ፤ ያስቀመጠ፤ የመነዘረ፤ የሸጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ ተብሎ የተደነገገ ሲሆን እነዚህ የተለያዩ ድርጊቶች በሕገወጥ መንገድ መነገድ ድርጊቶች ተብለው የተደነገጉ እና ወንጀል መሆናቸው ተደነግጓል። የተከሳሽን ድርጊት ከዚህ አንፃር ስንመዝነው ተከሳሽ በሱቃቸው ውስጥ የ 21 የውጭ አገራት ገንዘቦች የተገኙ ሲሆን ይህ ደግሞ የውጭ አገራት ገንዘብን የማስቀመጥ ድርጊት ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 346 ውስጥ የሚካተት ድርጊት ነው። ከዚህ ሌላ ተከሳሽ በፖሊስ ጣቢያ ቀርበው በሰጡት ቃል እነዚህን የተለያዩ አገራት ገንዘቦች ሲመነዝሩ እንደነበረ ያመኑ ስለሆነ በዚህ በድንጋጌው ስር የሚካተት ድርጊት ነው። የኢትዮጵያ ብር ተብሎ የተገለፀውን በተመለከተ ተከሳሽ በሱቁ ውስጥ ሕገወጥ በሆነ መልኩ የውጭ አገራት ገንዘቦችን እየመነዘሩ ስለሆነ ይህ ገንዘብም ለዚሁ ለሕገወጥ ስራው የሚያገለግል ወይም የሕገወጥ ስራው ውጤት ነው ከሚባል በስተቀር የግሌ ገንዘብ ነው የሚለው ተቀባይነት ያለው አይደለም። ተከሳሽ ከዚህ በላይ የተገለፁትን ሕገወጥ ድርጊቶች አለመፈፀማቸውን፤ በክሱ ላይ የተገለፁት የውጭ አገራት ገንዘቦች በሱቃቸው የተገኙበት ሁኔታ ተከሳሽን አያስጠይቅም ወይም ሕጋዊ ፍቃድ ነበረኝ የሚል፤ እንዲሁም በፖሊስ ጣቢያ ተከሳሽ ቀርበው ድርጊቱን መፈፀማቸውን ያመኑበትን ድርጊት የማስተባበያ አንድም ማስረጃ ያላቀረቡ ስለሆነ ተከሳሽን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 346 ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ተወስኗል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ የለንም፤ ነገር ግን ድርጊቱ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈፀመ መሆኑ ከግንዛቤ በማስገባት የሚያርምና የሚያስተምር ቅጣት እንዲወሰን በማለት አመልክቶ በተጨማሪም የውጭ አገር ገንዘቦቹ

እንዲወረሱ እንዲታዘዝልን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ፡</u> ዕድሜዬ 40 ዓመት ነው፤ ትዳርና ሁለት አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች አሉኝ፤ የትምህርት ደረጃዬ 9 ኛ ክፍል ነው፤ አሁን መተዳደሪያ የለኝም፤ ባለቤቴ ስራ የላትም በማለት ሲያመለክት ጠበቃቸው ደግሞ ባቀረቡት አስተያየት ተከሳሽ ለበርካታ ጊዜ ፍ/ቤት መመላለሳቸው፤ ዕድሜያቸው ወጣት መሆናቸው፤ የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆኑ፤ የራሳቸውን ቤተሰብና ሌሎችንም የሚረዱና የሚያስተዳድሩ መሆኑ፤ ወደፊት መልካም ዜጋ ለመሆን ዝግጁ መሆናቸው፤ ከዚህ በፊት በሌላ ድርጊት በሌላ ወንጀል የማይታወቁ መሆኑ ፍ/ቤቱ ከግንዛቤ በማስገባት በተከሳሽ ላይ ዝቅተኛ ቅጣት በመጣል፤ ቅጣቱንም በገደብ እንዲያግድልን እንዲሁም በዚህ ጉዳይ አራት ወራት ያህል የታሰሩ ስለሆነ ይሄው በቂ ነው እንዲባሉ በማለት አመለከተው፤ በሱቁ ውስጥ ከተያዘው ገንዘብ ውስጥ የኢትዮጵያ ብሩ የግል ገንዘባችንና በሱቁ ውስጥ ከምናካሂደው ንግድ ጋር የተያያዘ ስለሆነ እንዲመለስልን በማለት ገልፀዋል።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ኩበደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ

የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 346 /በህገወጥ መንገድ መነገድ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመበት የውጭ ሀገር ገንዘብ መጠን ከፍተኛ እና የበርካታ አገሮች ገንዘብ ስለሆነ፤ ይህ ደግሞ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው ጉዳትና ተፅዕኖ ከፍተኛ ስለሆነ የወንጀሉ ደረጃ ከባድ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 346 ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአንድ ዓመት ፅኑ እስራት እስከ አስር ዓመት ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000.00(ሃምሳ ሺህ ብር) በማይበልጥ መቀጮ ሲሆን፤ ቅጣቶቹ የእስራትና የገንዘብ ስለሆኑ ሁለቱም የቅጣት አይነቶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ለየራሳቸው መሰራት አለባቸው። በዚህም መሰረት የእስራት ቅጣቱን በቅድሚያ ስንወስደው የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት ከባድ ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከአምስት ዓመት ከስድስት ወር እስከ ሰባት ዓመት ከዘጠኝ ወር ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት ስድስት ዓመት ፅኑ እስራት መነሻ ቅጣት ተብሎ ተወስኗል።

ይህ በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ 1 እርከን 22 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቅድ ስልጣኑም/range/ ከአምስት ዓመት ከስድስት ወር እስከ ስድስት ዓመት ከሰባት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት ስድስት ዓመት ፅኑ እስራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስላላቀረበ ፍ/ቤቱ የመነሻ ቅጣት እርከኑን ከፍ አላደረገውም። በሌላ በኩል ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 መሰረት በማስረጃ የተደገፉ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላረቡ በመሆኑና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 መሰረት ደግሞ ፍ/ቤቱ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ያላገኘ ስለሆነ እንዲሁም በተከሳሽ በኩል የቀረቡት የቅጣት አስተያየቶች የቅጣት ማቅለያ ሳይሆኑ ፍ/ቤቱ በፍቅድ ስልጣኑ ውስጥ ለመንሸራሸር የሚያገለግሉ ስለሆኑ፤ ፍ/ቤቱ የመነሻ ቅጣት እርከኑን ዝቅ አላደረገውም። በመሆኑም

በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አባሪ አንድ እርከን 22 ላይ የተገለፀው መሰረት ተደርጎ የተወሰነውን ቅጣት ፍ/ቤቱ እንዳለ ወስዶታል።

በሌላ በኩል የግንዘብ መቀጮውን በተመለከተ ቅጣቱ የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት በመሆኑ፤ የወንጀሉ ደረጃ ከባድ ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ፤ ይህ ከሆነ ደግሞ በሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ ብር ሃምሳ ሺህ ብር ላይ አንድ ሦስተኛውን በመቀነስ በሚገኘው ውጤት ጣሪያና ቡበር ሃምሳ ሺህ ብር መካከል የሚወሰን ስለሆነ፤ ፍ/ቤቱም ከብር ሃምሳ ሺህ ሳያልፍ ቅጣቱን ይወሰናል። በዚህም መሰረት ፍ/ቤቱ ከተከሳሽ ገቢ አንፃር ያርመዋል፤ ያስተምረዋል ብሎ ባመነበት ቡበር 35,000.00(ሰላሳ አምስት ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 22 ላይ በተመለከተውና በተወሰነው መሰረት የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ባለመኖሩ በስድስት ዓመት ፅኑ እስራት እና ቡበር 35,000.00(ሰላሳ አምስት ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ተከሳሹ እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በማሰብ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት እንዲያስፈፅም ታዟል። ተከሳሽ ከዚህ ቀደም በዚሁ ጉዳይ በማረሚያ ቤት ለአራት ወራት ያህል ታስሬያለሁ በማለት የገለፀ ስለሆነ ይህንኑ በማጣራት በቅጣቱ ታሳቢ በማድረግ እንዲያስፈፅም ማ/ቤቱ ታዟል።

2 ኛ. የወንጀል ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ ከተከሳሽ ሱቅ የተያዙትና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአደራ የተቀመጠው የውጭ አገሮች ገንዘቦች በመንግስት እንዲወረሱ ታዟል። የኢትዮጵያ ገንዘብ ሆኖ ከተከሳሽ ሱቅ የተያዘው ገንዘብ ግን ተከሳሽ በሱቁ ውስጥ ይነግዱበት እንደነበር የገለፁ ስለሆነና ከምንዛሬው ወይም በህገወጥ መንገድ ከመነገዱ ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ዐ/ሕግ ያላስረዳ በመሆኑ ፍ/ቤቱም የህገወጥ መነገድ ወንጀሉ አካል ለመሆኑ ለመገመት ስላልቻለ እንዲሁም የኢትዮጵያ ገንዘብ መያዝ ደግሞ ወንጀል ባለመሆኑ፤ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 98 ም ይህንን ስለማይደግፍ ከተከሳሽ ሱቅ በወቅቱ የተወሰደው የኢትዮጵያ ገንዘብ የሆነው ብር ለተከሳሽ እንዲመለስለት ታዟል።

3 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

4 ኛ. ይህ የቅጣት ውሳኔ ዛሬ ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም ተነበበ።

5 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

6 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝጉብ ቤት ይመለስ።